# ምድብ አምስት (ከ10ኛ — 12ኛ) ክፍል
## 9 ኛ ሳምንት
## ምሥጢረ ንስሐ

**የቃሉ ትርጉም**

ንስሐ መመለስ ማለት ነው። ወደ እግዚአብሔር መመለስ። ንስሐ ለእርቅ የተዘረጋ የእግዚአብሔር እጅ ነው ንስሀ ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ስለራሳችን ንፅሕና ኃጢአትን መተው ነው።

**የትምህርቱ ዓላማ**

በዚህ ትምህርት ሁሉም ሰው ጸጸትና ኑዛዜ እንደሚያስፈልገው ኑዛዜ የእውነተኛ ጸጸት ማረጋገጫ ነው።

ሰዎች ኃጢአታቸውን አምነውና ለመታረምና ለማቆም ፈቃደኛ ሆነው ወደእግዚአብሔር መቅረብ ይገባቸዋል።

በዚህ ሂደት ንስሓ ሲፈጸም የምናገኘውን የእግዚአብሔር ፀጋና አፈጻጸሙን መማር የትምህርቱ ዋና ዓላማ ነው።

**የሚጠና ጥቅስ**

***«ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሓ ግቡ ተመለሱም»*** የሐዋ.ሥ 3÷19

**የምሥጢረ ንስሓ አጀማመር**

የተጀመረው በአዳም መጸጸት በእግዚአብሔር ምሕረት ሲሆን፣ ጌታችን በወንጌል በሦስት ቦታዎች ከክህነት ጋር አጣምሮ መስርቶታል።

1. ጴጥሮስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ካለው በኋላ ጌታችን ***‹‹ በምድር የምታሥረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል። በምድር የምትፈታው ሁሉም በሰማይ የተፈታ ይሆናል።*** ›› ማቴ 16.÷19 ሲል ቃል ገብቶለታል።
2. ለደቀመዛሙርቱ ቃል ሲገባላቸውም***«.....እውነት እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታስሩት በሰማይም የታሠረ ይሆናል÷ በምድር የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል።»*** ማቴ 18÷18፣
3. ከትንሳኤው በኋላም የሚጠብቃቸውን አብይ ተልዕኮ ሲነግራቸው «........ ***አብ እንደላከኝ እኔ እልካችኋለሁ አላቸው። ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ይቀርላቸዋል የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው።»*** ዮሐ. 20÷21-23፣

በዘመነ ሐዲስ «ንስሐ ግቡ» ብሎ በማስተማር ከሰባቱ ምስሶዎች አንዱ የሆነውን ንስሐን ከነአስፈፃሚዎቹ መሥራቹ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

**የትምህርቱ ይዘት**

በመጀመያ በኃጢአት በማዘን፣ በመጸጸት እና በመናዘዝ እግዚአብሔርን ይቅርታ መጠየቅ ይገባል።

ተነሳሂው(ዋ) ለካህኑ ሲናዘዙ ወደ እግዚአብሔር ይመለሳሉ።

ከዚያም በምክርና ፍትሐት (ይፍታህ ወይም ይፍታሽ) ከተባሉ በኋላ ቅዱስ ቁርባንን መቀበል ይጀምራሉ።

### የትክክለኛ ንስሐ መገለጫዎች፣

- ለተፈጸመው ኃጢአት ከልብ ማዘን (መዝ.6÷2-7)
- ወደ ኃጢአት ላለመመለስ ቁርጥ ውሳኔ መወሰን (የጠፋው ልጅ ሉቃ.15)
- በእግዚአብሔር ይቅር ባይነትና ምሕረት ማመን ፣
- ጌታ ***«ሂዱ ራሳችሁን ለካህናት አሳዩ»*** ሉቃ 17÷14 እንዳለን ለካህን መናዘዝ ።
- ከኃጢአት ምክንያቶች መጠበቅ። መዝ1÷1-3
- ሌሎችን ሳይከሡ እውነታውን ብቻ መናገር።
- ዳዊት ነቢዩ ናታንን እንደሰማው የካህኑን ምክር ማዳመጥና መቀበል። 2ኛ ሳሙ.12÷11-13
- ቅጣትን ለመቀበል መዘጋጀት 2ኛ ሳሙ 16÷9-14 ዕብ.12÷

### ንስሓ ለማን ነው?

ንስሓ የበደለ ሁሉ በእየዕለቱ ሊፈፅማት የሚገባ ምሥጢር /አገልግሎት/ ናት።

### በማን ይፈፀማል?

በተናዛዡ ኃጢአተኛ እና በካህኑ ሲሆን፣ የማሠር፣ የመፍታት ሥልጣን የሌለው ምሥጢር አይፈጽምም፣

- ተናዛዠው የታዘዘውን ከፈጸመ በኋላ ፍትሐት ዘወልድ /የንስሓ ጸሎት/ ተደግሞለት ከኃጢአት ይፈታል።
- ተናዛዥ ኃጢአቱን ሲናዘዝ ካህኑም ምክርና ቀኖና/ ቅጣት/ ለምክንያተ ድህነት ይሰጡታል። ለምሳሌ ስግደት፣ ምጽዋት፣ ጾም፣ ከምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ለተወሰነ ጊዜ መከልከል፣.......
- ተነሳሂው የተታዘዘውን ከፈጸመ በኋላ ፍትሐት ዘወልድ(የንሥሓ ፀሎት) ይፀለይለታል፣
- ከምዕመናን ጋር እንዲቀጠርም የጌታችንን ሥጋና ደም ይቀበላል።

<u>**ሁሉም ኃጢአት ይቅር ይባላል?**</u>

መጽሐፍ ቅዱስ የቱንም ያህል ከባድ ኃጢአት ይሠረያል ይለናል። ***«ኃጢአትና ስድብ ሁሉ ለሰዎች ይሰረይላቸዋል»*** ማቴ12÷31

***«ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፣ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን፣ እንደ አመዳይ ትነጻለች፣ እንደደምም ብትቀላ እንደባዘቶ ትጠራለች።»***ኢሳ.1÷18፣

- እግዚአብሔርም ሁሉንም ለመቀበልና ይቅር ለማለት ዝግጁ እንደሆነ ተምረናል

  ***«ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም»***ዮሐ 6÷37፣

- ለእኛ ትምህርት እንዲሆነን የተጻፉት የአባቶቻችን ታሪኮችም ይሄንኑ ይስገነዝቡናል።ለምሳሌ መዝሙረኛው ዳዊት ከባድ ኃጢአት ቢሠራም ይቅር ተብሎአል።ቅዱስ ጴጥሮስም ጌታን አላውቀውም ብሎ በንስሓ ተመልሶዋል። ማቴ.26÷69-75 ጌታችን ለሰቀሉት እንኳ ይቅርታ አድርጓል።

<u>**በምስጢረ ንስሓ በሚታይ አገልግሎት የምንቀበለው የማይታይ ጸጋ አለ።**</u>

<u>**የሚታይ አገልግሎት**</u>፣የተነሳሂው በካህን ፊት መናዘዝ፣ የካህኑ ቀኖና መስጠት እና ጸሎት፣ተነሳሒው የሚፈጽመው ቅጣት……..

<u>**የማይታይ ጸጋ**</u>፣ ከኃጢአት መፈታት(ሥርየተኃጢአት)፣ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ፣ ያጣነው መንፈሳዊ ኃብት መመለስ።

<u>**ማጠቃለያ፣**</u> ንስሐ ለሁሉም ጠቃሚና አስፈላጊ ምስጢር ስለሆነ፣ ዕለት ተዕለት ልንፈጽመው የሚገባ ሲሆን÷ ቅዱስ ቁርባን በመቀበል ከአምላካችን ጋር በአንድነት እንድንኖር ያግዘናል። ያስፈልገናልም፣፡

<u>**ተግባር**</u>

1. ሁልጊዜም ንስሓ መግባትና መቁረብ አለብን፣
2. ዛሬውኑ ንስሓ እንግባ፣
3. የንስሓ አባት ይኑረን፣

<u>**ኑዛዜ እና ጸጸት /ንስሐ/**</u>

- በቤተክርስቲያን ትምህርትና በክርስቲያናዊ ኑሮ ኑዛዜ የጸጸት ውጤት ነው።
- ከጸጸት የተለየ ኑዛዜ፣ ትረካ እንጂ ኑዛዜ አይደለም።
- ኑዛዜ ስለበደልነው በደል በፍጹም እምነት የምናቀርበው የጸጸት ውጤት ነው።
- ጸጸት ራስን መክሰስ እና በራስ ላይ መፍረድና ያንንም መቀበል ነው።
- እውነተኛው ጸጸት ከልብ ይጀምራል። ክፉ ሥራውን ሲተው - ጠባዩንም ያርማል፣እንጂ « በደለኛ ነኝ! » ብሎ መናገር ወይም መደጋገም አይደለም።
- ራሱን ክዶ ንስሀ የገባ ከእግዚአብሔርም ሆነ፣ ከሰው ማንኛውንም ቅጣት ሲቀጣ፣ ይገባኛል! ይላል፡፡
- ሲቀጡ ማጉረምረም ያለመጸጸት ማረጋገጫ ነው።
- ጸጸት የኃጢአት ውጤቶችን በተቻለ መጠን መተው ሲሆን፤ በሌሎች ያደረግነውን ፍትሕ አልባ ድርጊት ማረምም ነው።ለዚህም ነው ዘኬዎስ «ማንንም በሐሰት ከስሼ እንደሆንኩ አራት እጥፉ እመልሳለሁ።»ያለው ሉቃ.19÷9 አንተም የወሰድከውን መልስ የበደልከውን ካስ። ሳይክሱና የወሰዱትን ሳይመልሱ መጸጸት ብቻውን በቂ አይደለምና።
- ጸጸት፣ ትሑት ልብ ይፈልጋል። ለልዕልናና ክብሩ የሚጨነቅ አይጸጸትም፣
- ሁሌም ራሱን የሚከላከልና ለድርጊትና ንግግሩ መከላከያ በማቅረብ የሚሟገት ጸጸት የለውም። ክብሩ ከንስሓ ይመልሠዋልና ።
- ካህኑ ተነሳሂው መጸጸቱን ሲያይ « እግዚአብሔር ይፍታህ» ይለዋል ፣ «ይፍታህ» የሚባለው በኃጢአቱ የተፀፀተ ነውና፣
- መበደሉን በፍፁም ያመነ፣ ኀሊናው የሚወቅሰው፣ ጠባዩ ይታረማል፣ ይጸጸታልም። በተቃራኒው ራሱን በመከላከልና በማሳመን ብቻ የሚኖርም ከኃጢአቱ ጋር ይኖራል፣ ለዚህ ሰው ኃጢአቱ ምን ያህል ከባድ ቢሆንም አይረብሸውም።
  የሰዶም ሰዎች ዓይናቸው ታውሮ የሎጥን ቤት ደጃፍ ለማግኘት ሲፈልጉ ደከሙ የተባለው ለዚህ ነበር ዘፍ.19÷
- አንድ ሰው መሳሳቱን ካላመነ እንዴት ይጸጸታል? ሳይጸጸትስ እንዴት ይናዘዛል? በሰማያዊው ሥልጣን ያልተፈታስ እንዴት ከእግዚአብሔር ይታረቃል?
- ኃጢአትን ማመን የመጀመሪያ ደረጃ ÷ኑዛዜ ቀጣዮ ነው ። እውነተኛ ኑዛዜና ኃጢአትን አለማመን በጣም ይለያያሉ።

**ይቆየን።**